# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መጋቢት 7 ቀን 2004 ዓ.ም

## በዋልድባ ላይ ወያኔ ሊወስድ የተነሳውን እርምጃ ኢሕአፓ ያወግዛል

ሀገር አጥፊው የወያኔ አገዛዝ ታዋቂና ታሪካዊውን የዋልድባ ገዳም ለማፈራረስ በመነሳት የገዳሙን ለም መሬት ለቻይናውያን፣ ህንዶች፣ …ወዘተ ሊያከራይ/ሊለግስ ወስኗል። የዋልድባ ገዳም ቄሶችና መነኩሴዎች ሕይወታችን ሳትጠፋ መሬታችንን አንነጠቅም ፤ ገዳማችንም አይፈርስም ብለው ቆርጠዋልና ኢሕአፓ ጸረ-ሕዝብ የሆነውን ወያኔን እያወገዘ ለዋልድባ ገዳም ቀሳውስት ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል።

አረመኔው የመለስ አገዛዝ በሃይማኖቶች ላይ የአፍራሽና በታታኝ እርምጃ መውሰድ የጀመረው ገና ለሥልጣን ሳይበቃ መሆኑ የሚታውቅ ነው። ካድሬዎቹን ጳጳስና ሼክ እያለ ሰይሞ በተቋሞቹ ውስጥ ጉዳይም ጣልቃ እየገባ፤ እያሰረና እየገደለ (አንዋር መስጊድና አደባባይ ኢየሱስን መጥቀስ ይበቃል) ቆይቷል። የዘረኝነት መርዙንም ወደ ሃይማኖት ተቋሞች ማስገባቱንም አይተናል። ሙስሊም/ኢትዮጵያውያን እያካሄዱት ያለው ተቃውሞም የሚጠቀስ ነው። ወያኔ ሥልጣን ከያዘ በኋላ አጋሮቹ በሆኑ አክራሪዎች በርካታ ቀሳውስት የተገደሉባት የአሰቦት ገዳምም ጫካ በተከታታይ እየተቃጠለ ቢሆንም ወያኔ ይህንን ለማስቆም ምንም እርምጃ አልወሰደም።

የኢትዮጵያ ቅርስ የሆነውን ሁሉ ለማጥፋት የተነሳው ወያኔ በዋልድባ ገዳም ላይ የቃጣውን የጥፋት እርምጃ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲቃወምና እንዲያወግዝ ኢሕአፓ ጥሪውን ያስተላልፋል።


EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com